Temari.et

# Moral Education, 2017 EC, Grade 6 model exam

Grade 6 · Moral Education · 2017 E.C.

**Time allowed:** 120 minutes **Questions:** 34 **Total marks:** 34

Name ____________ Grade ________ ID No. ________ Date ________

**1.** ሀላፊነትን መወጣት ስንል ምን ማለታችን ነው? (1)

**A.** የሚጠበቅብንን ተግባር በአግባቡ ማሟላት ማለት ነው
**B.** ራሣችንን መጠበቅ ማለት ነው
**C.** ለምናደርገው ነገር ተጠያቂ መሆን ማለት ነው
**D.** ሁሉም

**2.** ከሚከተሉት ውስጥ ከግል ሏላፊነት ውስጥ የሚመደበው የቱ ነው? (1)

**A.** የሀገር ፍቅር ስሜት ማሳደግ
**B.** በጓደኛ አለመቅናት
**C.** ግብር በወቅቱ መክፈል
**D.** ህግና ደንብ ማክበር

**3.** ሀገራዊ ሀላፊነት ያልሆነው የቱ ነው? (1)

**A.** የግል ጤንነት መገንዘብ
**B.** ግብር በወቅቱ መክፈል
**C.** ህግና ደንብ ማክበር
**D.** የሀገር ፍቅር ስሜት ማሳደግ

**4.** የግል ሀላፊነት መወጣት የሚያመጣው አውንታዊ ውጤት ውስጥ የማይካተተው የቱ ነው? (1)

**A.** የቤተሰብ ደስታ
**B.** ለታናናሾች አርዓያ መሆን
**C.** እርስ በእርስ መጋጨት
**D.** የአዛውንቶች ምርቃት

**5.** ጠንካራ የስራ ባህል ምንን ይወክላል? (1)

**A.** እሴትን
**B.** ወግን
**C.** ልምድን
**D.** ሁሉም

**6.** ጠንካራ የስራ ባህል እንደ ሀገር ምን ጠቀሜታ አለው? (1)

**A.** የሀገር ፍቅር ስሜት እንዲኖር
**B.** በነፃነት ለመኖር
**C.** ብዝሀነትን ተቀብለን እንድንኖር
**D.** ሁሉም

**7.** የታታሪ ሠዎች ባህሪ ያልሆነ የቱ ነው? (1)

**A.** በጋራ ማጥናት
**B.** ስዓት ማክበር
**C.** ያልገባቸውን አለመጠየቅ
**D.** በክበባት መሳተፍ

**8.** አንድ ሠው በግብረገብ ምሉዕ ነው ሲባል ምን ማለታችን ነው? (1)

**A.** ታዛዥ ያልሆነ
**B.** ተግባሩና ምግባሩ ሲለያይ
**C.** ስነምግባር የጎደለው
**D.** ተግባሩና ምግባሩ ሲመሳሰል

**9.** ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የግብረገብ ምሉዕነት የተላበሠ ሠው መገለጫ ያልሆነው የቱ ነው? (1)

**A.** በራስ መተማመን
**B.** ርኅራሄ
**C.** ሀቀኝነት
**D.** ተለዋዋጭነት

**10.** ከሚከተሉት ውስጥ የግብረገብ ምሉዕነት ጠቀሜታ ያልሆነውን የቱ ነው? (1)

**A.** የሀገርን እድገት ያፋጥናል
**B.** ሙሠኝነት ይቀንሳል
**C.** ስርቆት ይጨምራል
**D.** የትምህርት ጥራት ይጨምራል

**11.** ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ህይወታችንን በምሉዕነት ለመምራት ይጠቅማል ? (1)

**A.** በገንዘብ ሀብታም ሆኖ መገኘት
**B.** ስኬታማ መሆን
**C.** የቤተሰብ እርካዳታ መጠበቅ
**D.** ሀቀኛ መሆንና በራስ መተማመን

**12.** በግብረ ገብ ምሉእነት ራሳቸውን የሚመሩ ሰዎች ያሉት ማህበረሰብ የሚያገኘው የቱ ነው? (1)

**A.** በሌሎተች ልፋት ጥቅም ማግኘት
**B.** ጠንካራ የስራ ባህል አላቸው
**C.** ማህበራዊ ግኑኝነት ጠንካ አለመሆን
**D.** ራሣቸው ከሌሎች አስበልጦ ማየት

**13.** ከሚከተሉት ውስጥ የታታሪ ተማሪ መገለጫ ያልሆነው የትኛውም ነው? (1)

**A.** የቤት ስራቸውን በሰአቱ ያጠናቅቃሉ
**B.** ከትምህርት ቤት ያለ አግባብ ይቀራል
**C.** በመማር ሂደት ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ያደርጋሉ
**D.** በተጓዳኝ ክበባት ይሳተፋሉ

**14.** ከሚከተሉት ውስጥ የጠንካራ የስራ ባህል ጠቀሜታ አይደለም? (1)

**A.** ከድህነት እና ከኋላ ቀርነት ለመላቀቅ
**B.** ለሀገር እድገት
**C.** ከጥገኝነት ለመላቀቅ
**D.** ተመፅዋች ለመሆን

**15.** ግላዊ እና ማህበራዊ አሰራሮችን ለመምራት ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ የማህበራዊ ቡድን መንፈሳዊና ቁሳዊ አካል ስብስብ ነው? (1)

**A.** ሀላፊነትን መወጣት
**B.** ግብረ ገባዊ ውሳኔ
**C.** ባህል
**D.** የተፈጥሮ ሀብት

**16.** ከሚከተሉት ውስጥ ህግን የሚገልፀው ጽንሰ ሃሳብ የትኛውም ነው ? (1)

**A.** ህግ ማለት ማንኛውም ማህበረሰብ ሊከተላቸው የሚገቡ የስነ ምግባር መርሆች ናቸው
**B.** ህግ የዜጎች ይሁንታ መገለጫ ነው
**C.** ህግ ለባለስልጣናት የተለየ ሆኖ ይዘጋጃል
**D.** ሀ እና ለ መልስ ናቸው

**17.** በፈቃደኝነት ህግን ላለመጣስ የሚደረግ ማንኛውም እንቅስቃሴን የሚገልፀው ሀሳብ የትኛው ነው ? (1)

**A.** ሙስና
**B.** ማጭበርበር
**C.** ለህግ ተገዥነት
**D.** የዝምድና ወገንተኝነት

**18.** ከሚከተሉት ውስጥ ለህግ መገዛት አስፈላጊነት ውስጥ የማይካተተው የትኛው ነው? (1)

**A.** ሠላምን ለማስፈን
**B.** ህገ ወጥ የህፃናት ዝውውር
**C.** ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍል
**D.** ሙሉ ነፃነት ማግኘት

**19.** ለህግ ተገዥ የሆኑ ዜጎች ከሚያሳይዋቸው ባህርያቶች ውስጥ አንዱን ምረጡ? (1)

**A.** የመብታቸውንና ሀላፊነታቸውን ገደብ ያውቃሉ
**B.** የሀገሪቱን ህግ መጠበቅ የህዝቦችን ይሁንታ መጠበቅ እንደሆነ ያምናሉ
**C.** ህግን አለማወቅ ከቅጣት እንደማያድናቸው ይገነዘባሉ
**D.** ሁሉም መልስ ናቸው

**20.** ከህጎች መስፈርቶች ውስጥ የማይካተተው የትኛውም ነው? (1)

**A.** ቋሚ
**B.** ወጥነት
**C.** ተለዋዋጭነት
**D.** ኢ_ ፍትሃዊነት

**21.** ዜጎች እና የህዝብ ተመራጮች ለህግ የማይገዙ ከሆነ ምን አይነት አሉታዊ ተጽእኖ ይኖራል? (1)

**A.** ሉአላዊነትን ማስጠበቅ
**B.** ሙሉ ነፃነት ማግኘት
**C.** የሠላም እጦት
**D.** ሀ እና ለ መልስ ናቸው

**22.** ከሚከተሉት ውስጥ የሙስና መገለጫ ያልሆነው የትኛው ነው? (1)

**A.** ህግን መሠረት አድርጎ መስራት
**B.** ማጭበርበር
**C.** ጉቦ መስጠት
**D.** የዝምድና ወገንተኝነት

**23.** ከተሠጡን በርካታ አማራጮች ውስጥ ትክክለኛና የተሻለውን የመምረጥ እና የመወሰን ሂደት ነው? (1)

**A.** በራስ መተማመን
**B.** ግብረ ገባዊ ውሳኔ አሠጣጥ
**C.** ለህግ ተገዥነት
**D.** የግብረ ገብ ምሉዕነት

**24.** ተማሪ በረከት የ6ኛ ክፍል ተማሪ ሲሆን በመንገድ ላይ በጣም ቸኩሎ እየሄደ አስፋልት ለመሻገር የተቸገሩ አዛውንት ይመለከታል። ምን አይነት ግብረ ገባዊ ውሳኔ መወሰን አለበት? (1)

**A.** በጣም ስለቸኮለ እያያቸው ጥሏቸው መሄድ
**B.** እጃቸውን ይዞ ማሻገር
**C.** ለመሄድ ያሰበበት ቦታ ይሄድና ሲመለስ ማሻገር
**D.** መልሱ የለም

**25.** ከሚከተሉት ውስጥ የግብረ ገባዊ ውሳኔ አሠጣጥ ችሎታ ባህርያት ውስጥ የሚካተተው የትኛውም ነው? (1)

**A.** ምክንያታዊነት
**B.** ምክንያታዊ ውሳኔ
**C.** አሳቢነት
**D.** ሁሉም መልስ ናቸው

**26.** ትክክለኛ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ የማይካተተው የትኛው ነው ? (1)

**A.** ችግሩን መለየት
**B.** መወሰን እና መከታተል
**C.** ሊከሰቱ የሚችሉ ውጤቶችን መለየት
**D.** መልስ የለም

**27.** ከሚከተሉት ውስጥ የግብረ ገባዊ አሠጣጥ ተግዳሮት ያልሆነውን ምረጥ ? (1)

**A.** የአቻ ግፊት
**B.** ለራስ የሚሰጥ ግምት
**C.** የተገደበ ምክንያታዊነት
**D.** አሳቢነት

**28.** ያለንን እምነት ለሚያረጋግጡ መረጃዎች ትኩረት የመስጠትና ካለን እምነት ጋር የሚጋጩ ችላ የማለት ወይም የመቀነስ ዝንባሌ ምን ይባላል? (1)

**A.** የማረጋገጫ ወገንተኝነት
**B.** ተጨማሪ ቁርጠኝነት
**C.** የበዛ ቁርጠኝነት
**D.** የግንኙነት ግጭት

**29.** ሰዋች እምነቶቻቸውንና አውንታዊ አስተሳሰባቸውን በድርጊት ሲፈፅሙ ምን አይነት ባህሪ ይኖራቸዋል? (1)

**A.** በሠዋች ዘንድ ተቀባይነት የሌለው ባህሪ ይኖራቸዋል
**B.** መልካም ባህሪ ይኖራቸዋል
**C.** ለህግ የማይገዛ ሰው ባህሪ ይኖራቸዋል
**D.** ሀ እና ሏ መልስ ናቸው

**30.** ከሚከተሉት ውስጥ መልካም ባህርይ ያለው ሰው መገለጫ የሆነው የቱ ነው? (1)

**A.** ተጠያቂነት
**B.** ምሉዕነት
**C.** ሀቀኝነት
**D.** ሁሉም መልስ ናቸው

**31.** አላስፈላጊ ውስጣዊ ግፊትን፣ስሜትን እና ምኞትን መቆጣጠርን የሚገልፀው ሀሳብ የትኛው ነው? (1)

**A.** ሀቀኝነት
**B.** ራስን መቆጣጠር
**C.** ትሁት መሆን
**D.** በራስ መተማመን

**32.** የመልካም ባህሪ ባለቤት መሆን ምን አይነት ጠቀሜታ አለው? (1)

**A.** በህብረተሠቡ ዘንድ ክብርና ተቀባይነት ለማግኘት
**B.** በሰዋች ዘንድ እምነት ያሳጣል
**C.** ለተለያዩ ቅጣቶች መዳረግ
**D.** ሁሉም መልስ ናቸው

**33.** መልካም ባህርይ ማሳደጊያ መንገዶች ውስጥ የማይካተተው የትኛውም ነው? (1)

**A.** ኀላፊነትን መወጣት እና እራስን ለተጠያቂነት ማዘጋጀት
**B.** የግጭት ዝንባሌን ማስወገድ
**C.** ታማኝ መሆን እና የገቡትን ቃል መጠበቅ
**D.** የሰዎችን ክብር መንፈግ

**34.** አንድ ሰው መልካም ባህሪ ከሌለው ምን አይነት አሉታዊ ተጽእኖ ይደርስበታል? (1)

**A.** ብቸኛ መሆን እና መገለል

**B.** ታማኝ አለመሆን

**C.** በቤተሠብ፣በጓደኛ እና በህብረተሠቡ ዘንድ ተቀባይነት ማጣት

**D.** ሁሉም መልስ ናቸው

— END OF EXAMINATION —